


# የፍቅር መልዕክቶች



መጋቢት 2017
ቅፅ ፫ | ቁጥር ፩

ንስንስ ትኩረቷን በLBQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ በኩዊር ኢትዮጵያ የምትታተም መጽሔት
Nisnis - A quarterly magazine published by Queer Ethiopia focusing on LBQ issues

# QUEER ETHIOPIA
# ኩዊር ኢትዮጵያ

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ'ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።



queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

t.me/queeret



# ማውጫ


የአርታዒያን መልዕክት 03

ግን እንኖራለን? ? 04 - 05

በቡና እና በመፅሃፍት መሃል 06- 09

ይድረስ በሚስጥር 10-11

ደብዳቤ ወደቤተክርስቲያን ሰዎች 12 - 13

ባልተመለሰ ፍቅር 14 - 15

የመሬት መንቀጥቀጥ ያህል 16 - 19

ምስጋና ብርቱ 20-21

ለራስዎ የፍቅር ደብዳቤ ፃፉ 22-24

# የአርታዒያን መልዕክት

ርዕስ አንቀጽ

ውድ አንባቢዎቻችን

ይህ የንስንስ እትም የፍቅር ደብዳቤዎች ስብስብን ይዞላችሁ መጥቷል። እነዚህ ደብዳቤዎች ለፍቅረኞቻችን፤ ለራሳችን፤ ለወደፊታችን እና ለሌሎችም የተፃፉ ናቸው።

ከዛ በፊት እኛ ለእናንተ የጻፍነውን ደብዳቤያችንን እንድታነቡልን ጋበዝን።

የንስንስን አስራ አምስተኛ እትም ስናሳትም ያለነው በእናንተ መኖር እንደሆነ በማስታወስ ነው። ስለመጀመሪያ ፍቅራችሁ፤ በምርጫ ስላገኛችኋቸው ቤተሰቦቻችሁ፤ እና ማንነትን ስለመቀበል ብዙ ታሪኮችን አጋርታችሁናል። አምናችሁን የእውነታችሁ አካል ስላደረጋችሁን ይህን ማህበረሰባችንን ደማቅ እንዲሆን ሆኗል። እናመሰግናለን።

እናያችኋለን። ዝም ሊያስብላችሁ እና ሊያጠፋችሁ በሚሞክር አለም ውስጥ በትጋት እንደምታፈቅሩ እናያለን። የህይወትን ውጣ ውረድ በጽናት እና ጸጋ ስታሳልፉ እንመለከታለን። ራሳችሁን ሆናችሁ ለመኖር ያላችሁ ጥንካሬ ብቻውን አብዮት ነው። ፍቅር፤ በሁሉም ሁኔታ ውስጥ አብሮነታችንን የሚያጠናክር እንደሆነ ያስታውሰናል።

በእነዚህ ገጾች ኩዊር ታሪኮች የሚከበሩበትን ቦታ እየገነባን ነው። ደስታችን ተቃውሟችን የምንገልጽበት እና ማንም ሰው ብቻውን ሊሆን እንደማይገባ እናሳይበታለን። የእናንተ ብርሀን፤ ለየት ብሎ ደምቆ የሚታየው መኖራችሁ ትልቅ ዋጋ አለው።

ወድ ቤተሰቦቻችን ኑሩልን። ድመቁልን። ተዋደዱ። ከመጀመሪያ እትማችን እስከአሁኑ ስኬታችን ድረስ እምነታችሁ ጠብቆ እንዳኖረን አትርሱ። በዚህ ጉዞአችን መቼም ብቻኛ አይደለንም።

ከፍቅር እና አብሮነት ጋር
ኩዊር ኢትዮጵያ

# ግን እንኖራለን? የፍቅር ደብዳቤ ለመኖር እና ለተስፋ

ውድ የወደፊቷ ቪያ

የጥላቻ መርዝ በአለም ተንሰራፍቶ በወንዶች ልብ ውስጥ ቦታ እየያዘ ነው። ይህ ጥላቻ በአለም ላይ ፍርሀትን እያሰፈነ፤ ፍርሀቱ ደግሞ በውስጤ እያደገ እና ስለነጻነቴ እና ደህንነቴ እንድሳቀቅ እያደረገኝ ነው።

ማወቅ እፈልጋለሁ። ማወቅ አለብኝ። ነገሮች ወደፊት ይሻሻላሉ?

የት ነው የምንኖረው?

ሳን ፍራንሲስኮ ባህር ዳርቻ ላይ ያለ ቤት ነን? ሰፊ መስኮት አለው? ብዙ አትክልቶች አሉን? የፕራይድ ባንዲራ በራችን ላይ ተሰቅሏል?

ታይላንድ ነን? ባንግኮክ ውስጥ ያለ አፓርትመንት እየኖርን ነው? ከተማዋ ለሊቱን አትተኛም አይደል? ጨረቃዋ በምሽቱ ሰማይ ደምቃ ትታያለች? ቀኖቻችንን ደምቀን የምንኖረው ማታ ላይ ነው?

መኖራቸው ነጻነትን እና መታፈንን እንዲሰማን የሚያደርጉንን እነዛን አዲስ አበባን የከበቧትን ተራሮች ከነስስ አየርና ቅዝቃዜያቸው እንናፍቃቸዋለን? ጥለነው መሄድ የምንፈልገውን ያህል መመለስን እንመኛለን? ያ መቅሰፍት የሆነ ናፍቆት አሁንም መልካም መልካሙን እንጂ የስምጥ ሸለቆውን ትካዜ አያስታውሰንም?

ቤታችን ውስጥ ፍቅር አለ? የሀበሻ አይነት በአንዴ ብዙ የሆነው ፍቅር ነው? በፈገግታ ስር መገማመት ያለበት፤ ማንነታችንን የምንደብቅበት፤ በፍርሀት ታስረን የጓደኞቻችንን ስህተት የምናሳልፍበት እና ሲልም የምንስማማበት ድብብቆሽ ውስጥ ነን?

የኲዊር ፍቅር ነው? ቤተሰባዊነት የደም ሳይሆን ፈልገን ያገኘነው ነው? ቤታችን በብሎኬት እና ሲሚንቶ ሳይሆን ሁሉንም ማንነት እና ስያሜ በሚጠይቁ ሰዎች ሲጋና ደም የተገነባ ነው?

ጥሩ ምግብ አለን? የምናጋራቸው ጥሩ ሰዎች አሉን ?

እሁን ከሀንግኦቨር ራሳችንን የምናስታምምበት እና ለሚቀጥለው ሳምንት ስራ ራሳችንን የምናሳርፍበት ነው?

የሚያውቅ ሰው አለ? እማዬ? አባዬ?

ከዚህ እንወጣለን?

ልቤ ውስጥ ብዙ ጥያቄዎች አሉ።

አሁን ማን እንደሆንን እና የት እንዳለን ጠይቃለሁ።

በዙሪያችን ስላሉ ሰዎች እና ስለምንገነባው ማህበረሰብ።

ግን እንደምንኖር ተስፋ አደርጋለሁ፤ መትረፍ ሳይሆን የእውነት መኖር።

ያለይቅርታ በኩራት ኲዊር እንደሆንን

በሚያጋጥመን ጨለማ ውስጥ የሚበራ ብርሀን እንዳለን ተስፋ አደርጋለሁ።

በቁማችን ሊቀብረን ከሚፈልገው ጥላቻ ልቀን፤ መኖራችንን ከሚጠሉ ሰዎች ተሽለን እንኖራለን።

ከፍቅር ጋር

የአሁኗ ቪያ



“ጥለነው መሄድ የምንፈልገውን ያህል መመለስን እንመኛለን?”



# በቡና እና በመፅሃፍት መሃል፡ ከኩዊር አጋር የተፃፈ ማስታወሻ



የፍቅር ደብዳቤ ከአጋራችሁ

ኩዊር ቤተሰቦቼ

እንዴት እና መቼ አጋራችሁ እንደሆንኩ አላስታውስም። እውነት ለመናገር ድንገተኛ ውሳኔ ይሆን ወይም ሁሌም የነበርኩት ነገር አላውቅም። በፊት እና በኋላ ብዬ የምገልጸው ጊዜ የለኝም፤ የሆነ ቀን በርቶልኝ እና በውስጤ የነበረውን ጥላቻ ገፍፌ ወደመቀበል የሄድኩት ጉዞ አልነበረም።

እንዲሁ... ምንም ልክ ያልሆነ ነገር አላችሁ ብዬ አስቤ አላውቅም።

ትንሽ ይገርማል አይደል; የተወለድኩት ኢትዮጵያ ነው።  በባህል ስም ሰው ከተሰመረለት መስመር ትንሽ እንኳን ወጣ ካለ ደህንነቱ በማይጠበቅባት ኢትዮጵያ።  ለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ያለን ጥላቻ በነጻነት የሚነገርበት ሀገር ነው፤ ሰዎች ቀለል አርገው ቡና እየጠጡ በፈገግታ እናንተን ስለማሳደድ እና መግደል ያወራሉ። በሹክሹክታም አይደለም፤ አያሳፍራቸውም፤ የሚናገሩት በጩኸት እና በኩራት ነው።

እንደዛም ሆኖ ይሄ አስተሳሰባቸው ውስጤ አልቀረም። ልጅ እያለሁ ለእናንተ ስም አልነበረኝም፤ ያደግኩት ያለኢንተርኔት ነው። ኢንተርኔት ያለው ስልክ ስይዝ አስራ አንደኛ ክፍል ነበርኩ። 15 ወይ 16 አመት ቢሆነኝ ነው። ያኔም ግን ስለኪውር የሚናገር ምንም መረጃ

**“በዚህ ጉዞ ብቻችንን እንዳልሆንን እንዳልረሳ ያደርገኛል። የሚወዱን፤ የሚያስቡልን እና እውነታችንን የሚቀበሉ ሰዎች አሉ።“**





ያጋጠመኝ አይመስለኝም።

ግን ሳላውቃችሁም ጠልቻችሁ አላውቅም።


ያዳኑኝ መፃህፍት ይመስሉኛል። ቃሉን ከማወቄ በፊት ማንበብ ርህራሄን አስተምሮኝ ነበር። የሚሰጡኝን መልሶች ሁሉ ከመቀበል ይልቅ መጠየቅን ተምሬበታለሁ። ሰዎች ከሚታዩት በላይ የየራሳቸው ታሪክ እንዳላቸው፤ ለሁሉም ነገር ምክንያት እንዳለሁ እንድረዳ አድርጎኛል።

ባነበብኳቸው ገጾች ውስጥ ፍቅር፤ እውነተኛ ፍቅር ከማእቀብ ጋር እንደማይመጣ ተማርኩ።

ሀይማኖተኛ ሆኜ አላውቅም። ልጅ እያለሁ ቤተሰቦቼ ይወስዱኝ ስለነበር ቤተክርስቲያን እሄድ ነበር ግን እምነት ውስጤ ሰርጾ አልገባም። አንዳንዴ አማኝ ብሆን ኖሮ ስለእናንተ ያለኝ ስሜት የተለየ ይሆን ነበር ብዬ አስባለሁ፤ ግን ደግሞ በፈጣሪ የማምን ቢሆን ፈጣሪም ይወዳችሁ ነበር ብዬ አላስብም?

ከቁጥጥር ይልቅ መልካምነትን የሚያስቀድም ፈጣሪ አይኖርም?

ኢትዮጵያ ውስጥ ግን አጋራችሁ መሆን ራሱ አደገኛ ነው። “አልጠላቸውም” ብሎ መናገር እንኳን እንደኑዛዜ ሊወሰድ ይችላል።  ብዙ የማውቃቸው ሰዎች፤ የምወዳቸውን ጨምሮ በኩራት የኩዊር ጥላቻ ያለባቸው ናቸው። ጥላቻ ጸድቅ ነው ብለው



“ባነበብኳቸው ገጾች ውስጥ ፍቅር፤ እውነተኛ ፍቅር ከማእቀብ ጋር እንደማይመጣ ተማርኩ።”



ማመን ይቀላቸዋል ስለዚህ ለደህንነቴ እና ለሰላም ስል ርእሱን አንስቼ አላዋራቸውም። በህይወቴ የማምናቸው ጥቂት ሰዎች ብቻ ስለአቋሜ ያውቃሉ።

እንደዛም ሆኖ ቀላል አይደለም። ርእሱ ከተነሳ መምረጥ አለብኝ። ልከራከር? ላስረዳ? የምትወዱት ኢየሱስ ሁሉንም እንደራሳችሁ ውደዱ ብሏችኋል ልበላቸው? ኩዊር መሆን ሀጥያት ነው ብለው ካሰቡስ እንደአማኝነታቸው ማድረግ ያለባቸው መጸለይ እንጂ መግደል ነው?

ግን ይህን ንግግር ማድረግ መጨረሻ አይኖረውም። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ ቀለል አድርጌ "ባትስማሙበትም ሰውን እንደፈለገ እንዲሆን ለምን አትተውም? ባትረዱትም ባትወዱትም ቢያንስ ጥላቻ አትዝሩ" እላለሁ። በጣም ትንሽ ነገር ነው ግን እንደዛም ሆኖ ለኢትዮጵያ ከባድ ጥያቄ ይመስላል

ይህን ደብዳቤ የምጽፍላችሁ ብቻችሁን አይደላችሁም ለማለት ነው። ሁላችንም እናንተን ለመጉዳት አንፈልግም። አንዳንዶቻችን አዲስ ነገር እየተማርን፤ የምናውቀውን እየተውን፤ አለምን እንድናይበት የተሰጠንን መነጽር እየቀየርን ነው። ስለልምዳችሁ፤ ስለህይወታችሁ፤ ኢጋራችሁ መሆን ምን ማለት እንደሆነ፤ ጥግ ላይ ሆኖ ከመስማማት በላይ መሆን እንዳለበት ብዙ መማር ያለብኝ ነገር እንዳለ እርግጠኛ ነኝ። ግን የማላውቀው ብዙ እንዳለ ሆኖም፤ አንድን ነገር ግን አውቃለሁ። ፍቅር ይገባችኋል። ደህንነት ይገባችኋል። በድብብቆሽ ሳይሆን ከነሙሉ ማንነታችሁ መኖር ይገባችኋል።

በአደባባይ ልናገረው ባልችልም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እንኳን የሚደግፏችሁ ሰዎች እንዳሉ እወቁ። ከብዙ ፍቅር እና ፍቅር አንድ ቀን ከጥላቻ የበለጠ ሀይል እንደሚኖረው ተስፋ በማድረግ።

# የዘጠኝ አመታት ፍቅር ደብዳቤ



## የኔ ፍቅር

ዘጠኝ አመታት። በድብቅ የመውደድ፤ ሰው በተጠራጠረ ቁጥር የመደናገጥ፤ ልቤ ከጓደኛ በላይ መሆንሽን እያወቀ ለሰው የማስመሰል ዘጠኝ አመታት። የተሰረቁ ቅጽበታት፤ በጆሮ የተነገሩ ቃላቶች፤ ቦታ አልሰጣችሁም ባለን አለም ላይ ማፍቀርን የመማር ዘጠኝ አመታት።

ቀላል አልነበረም። ዝምታን ተሸክመናል፤ መገኘትን ፈርተናል። የእኛን አይነት ፍቅር ከሚያጥላሉ ሰዎች ጋር ፈገግ ለማለት ተገደናል፤ መኖሩን የማያውቁትን እኛነታችንን ለመደበቅ ዝም ብለናል። ሚስጥራችን እስኪያፍነን ድረስ ከባድ ቀናትን አሳልፈናል፤ በአደባባይ እወድሽ እንደሁ አስቤ አውቃለሁ።

ጓደኞች አጥተናል። ከጎናችን ሆነው ሳቅና ትውስታ የተጋሩን ሁሉ እውነቱን ማወቅ ሲጀምሩ ሸሽተውናል። ሌሎች ጀርባቸውን ሰጥተውናል፤ በሚዋጉ ቃላቶቻቸው አድምተውናል። በአይታቸው ፍቅራችን ልክ እንዳልሆነ፤ መጥፋት ያለበት እንደሆነ ነግረውናል። በዚህ ሁሉ ክህደት፤ ፍርሀት፤ የዝምታ እምባ ውስጥ አንድ ነገር ብቻ አልተቀየረም። እኛ። ዛሬም አለን። ዛሬም እርስበርስ እንደተመራረጥን፤ የመጀመሪያ ቀን የነበረ ፍቅራችንን እንደያዝን አለን። ባይሆን ላንቺ ያለኝ ፍቅር ጨምሯል። አለም ሊያየን በሞከረ ጊዜ ሁሉ ላንለያይ አብረን ብዙ በማሳለፋችን ከመቼውም በላይ እወድሻለሁ።


የተለየ አለምን የምናፍቅባቸው ቀናት አሉኝ። በነፃነት እጅሽን ይዤ የምራመድበት፤ ፍቅራችን የሚደበቅበት ሳይሆን የሚከበርበት፤ በኮድ እና በድብብቆሽ ሳይሆን በግልጽ የምናወራበትን አለም እመኛለሁ። ይህ አለም ባይኖረንም ግን እኛ አለን። አንዳችን ለአንዳችን አለን። ከየቱም ህግ፤ ከየቱም ጥላቻ የሚልቀው ፍቅራችን ዛሬም አለ።

ወደፊታችን ምን ይዞ እንደሚመጣ አላውቅም። የማውቀው ግን በማንኛውም ህይወት ውስጥ፤ በሁሉም አለም፤ በምችለው መንገድ ሁሉ እወድሻለሁ። ሁኔታዎች ባይፈቅዱም፤ የሚገድበን ቢበዛም ደግሜ ደጋግሜ እመርጥሻለሁ።

አንድ ቀን የማንደበቅበት አለም ውስጥ እንደምንነቃ ተስፋ አደርጋለሁ። ለሁሉም ሰው በኩራት ምን ያህል እንደምወድሽ መናገር የምችልበት አለም። እስከዛው ግን በጸጥታ፤ በትጋት፤ በማያልቅ ፍቅር እወድሻለሁ።

ምክንያቱም የኔ ፍቅር... ሁሉም ይገባሻል።

ያንቺው
ዛሬም ወደፊትም



# ደብዳቤ ወደቤተ



ይድረስ ለቤተእምነት

ይሄንን ደብዳቤ የፃፍኩት በጭላንጭል ተስፋ ነው። ያደግኩት ቤተእምነት ውስጥ ነው፣ ይህ ስፍራ ፍቅርን፣ ድጋፍን እና መፅናኛን ለመስጠት ታስቦ እንደሆነ በደንብ አምንበት ነበር። ነገር ግን እንደኩዊር የራሴን ማንነት እየተረዳሁ ስመጣ፣ ይህ ለመፅናኛ የሚሆን ቦታ ብዙውን ጊዜ የጉዳቴ ምንጭ እንደሆነ በፍጥነት ተረዳሁኝ።

ስለማንነቴ ከቤተእምነት በተዘዋዋሪ የደረሰኝ መልእክት በጣም ግልጽ ነበር፡፡ ሃጢያተኛ እንደሆንኩ፣ ፍቅር የማይገባኝ እና ከሁሉ በታች እንደሆንኩ አሳውቀውኛል። ማንነቴ ከአምላክ ፍቅር እንድገለል ይገባኛል ብዬ በማመን ለብዙ ዓመታት የዚህን ውድቅነት ክብደት ተሸክሜያለሁ። ስብከቶቹ፣ ሹክሹክታዎቹ፣ ትምህርቶቹ ፤ ሁሉም ፍቅሬ ርኩስ መሆኑን አጠናክረውታል። ለመውደድ እና ለመወደድ ለሚፈልግ ሰው፣ እነዚህ ቃላት ልቋቋማቸው ያልቻልኳቸው ሸክም ነበሩ።

በአንድ ወቅት የጦር ሜዳ መስሎ በነበረ ቦታ መትረፍ፣ መገንባት እና ሰላም ማግኘት እንደሚቻል ሕያው ማስረጃ ነኝ። ብቻ ግን ተርፌያለሁ። ምንም እንኳን ጉዳት ቢደርስብኝም ፣ ጥላቻ ቢኖርም፣ እኔ ተርፌያለሁ። በብቸኝነት ውስጥ ፅናትን፣ ጥንካሬን እና የእምነቴን ጥልቅ ግንዛቤ አገኘሁ። እምነቴም ብዙውን ጊዜ ከመድረክ ላይ በሚሰበኩ ጠባብ አመለካከቶች ያልተገደበ ነው።

ዛሬ ላይ ፍቅር፣ እውነተኛ ፍቅር፣ በስርዓተ ፆታ ወይም ወሲባዊ ማንነት ያልተገደበ መሆኑን ጠንቅቄ አውቃለሁ። ፍቅር መለኮት ነው።

ታሪኬን የማካፍለው ለማውገዝ ሳይሆን የሚያገሉ፣ የሚፈርዱ

# ክርስቲያን ሰዎች



እና የሚጎዱ ትምህርቶች ያደረሱትን ጉዳት ግልጽ ለማድረግ ነው። በእነዚህ መልእክቶች የተተወው የስሜት ጠባሳ ቀላል አይደለም:: ብዙ ኩዊር ሰዎች በቤተእምነት ተቀባይነት በማጣት ምክንያት እራሳቸውን ለመጉዳት፣ ለማግለል ወይም ለከፋ፣ ተገደዋል። በእምነት ቦታዎች የምንሰማቸው ቃላቶች እኛ ነን ብለን የምናምንበትን ሰው ይቀርፃሉ:: እና ለብዙ ጊዜ፣ ቤተእምነት እንደተሰበርን፣ ህብረት እንደማይገባን አስተምራናለች።


ህብረት ይገባናኛ:: አባልም ነን። ሁሌም ነበርን:: ፍቅራችን የተቀደሰ ነው። ህልውናችን የተገባ ነው። እና የትኛውም ቤተ እምነት፣ የትኛውም ማህበረሰብ፣ የትኛውም ትምህርት ከእኛ ሊወስድብን አይችልም።

ከአመታት ጥላቻ በኋላ የፈውስ ጉዞው እየቀጠለ ነው፣ ራሴን ሙሉ በሙሉ መውደድን ተምሬአለሁ፣ ኩዊርነቴን እንደ ውብ፣ የማንነቴ ወሳኝ አካል አድርጌ መቀበል ችያለሁ። እናም በዚህ ጉዞ ውስጥ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር ሁኔታዊ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ—ፍቅሩ ሰፊ፣ አካታች እና የማይናወጥ ነው።

ቤተ እምነቶች ፣ አስተምህሮዎ ያስከተለውን ጉዳት እንደገና እንዲያጤኑት እናፍቃለሁ። ቤተ እምነት እሰብካለሁ የምትለውን የፍቅርና የመቀበል መልእክት በትክክል የምትይዝበት ጊዜ እንዲመጣም እመኛለሁ። እኛ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የምንወደድበት እና ሁሉንም ሰው የምንቀበልበትን ቦታ የምንፈጥርበት ጊዜ እንዲመጣ እፈልጋለሁ: እጓጓለሁም:: በተለይ ደግሞ እንደእኛ የተገለሉት እና የተፈረጀባቸውን የምትሰበስብበት ጊዜ እናፍቃለሁ።

አንድ ቀን ቤተክርስቲያን የእውነተኛ መቅደስ ትሆናለች ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ:: ፍቅር ያለገደብ እና ለሁሉም በነጻ የሚሰጥበት ቦታ ሆና ባያት እመኛለሁ። ለዚያ ፍቅር ደግሞ እኛ ኩዊር ሰዎችም የተገባን ነን።

# ባልተመለሰ ፍቅር ውስጥ የተገኘ ታላቅ ስጦታ



ውድ የመጀመሪያ ፍቅሬ

አሁን ካየውህ አራት አመታት እየሞላን ነው። ምንኛ የሚያሳዝን ቢሆንም ግን የህይወት አንዱ ክፍል ነው ተቀብዬዋለው እንኳን አለመተያየታችንን ቀርቶ እኔን ማፍቀር አለመቻልህን የተቀበልኩ ሰው ነኝ እንደ እኔ ሆነህ አልተፈጠርክም አንተ እንደ ራስህ ነህ ለሴት ነው ፍቅር ያለህ

አንተን ለመጀመሪያ ጊዜ ካየውበት ጊዜ ጀምሮ ወድጄህ ነበር ምናልባት ቁኝጅናህ ይሆናል የማረከኝ ከዛ እየቆየው ሳውቅህ የእኔን ስሜት ከተረዳህ በኋላ አለመለወጥህ የበለጠ እንዳከብርህ አደረከኝ ብዙ ቀጦች ስለ እኔ ካወቁ በኋላ ለመለወጤ ነበር የተጉት አንተ ግን የእኔ ወንድ አፍቃሪ መሆኔን መለወጥ አልፈለክም ራስህን ሁን የሚለው ቃልህ ጠቅሞኛል ለውጦኛል

ፍቅር ማውቅ ይመስለኝ ነበር ነገር ግን አንተን መውደዴ ውስጤ የነበረውን ራስን መጥላት አጠፋው ፍቅርህ እያየለብኝ ሲመጣ ውስጤ የተጠቀጠቀው ጥላቻ እና ሀዘን ቀስ እያለ መጥፋት ጀመረ ልክ ቆሻሻ ውሃ የሞላበት ብርጭቆ ነበርኩ ነገር ግን ፍቅር ውስጤን ሲሞላው እየጠራው መጣው።

ከዚህ በላይ ፍቅረ ምን አለ ውስጣችን ያለ ቆሻሻን ከማፅዳት የበለጠ ፍቅር የት አለ!

ማን ያውቃል አንተ ግድ የለሽ ሆነህ ይሆናል እንደ ሙድህ ያልከኝ ነገር ግን የእኔ እንደ ሙድ መሆንን መፍቀድህ የበለጠ ራሴን እንዳይ አደረከኝ። አንተ አይደለህም የለወጥከኝ እውነት ለመናገር ነገር ግን ላንተ ውስጤ የተፈጠረው የመውደድ ስሜት እንጂ አይኞቼን የከፈታቸው።

ነገር ግን ላመሰግንህ ወዳለው ላሳየኸኝ ቀናነት እና ራሴን የመሆንን ስፍራ ያለ ወቀሳ እንድነግርህ ስለፈቀድክልኝ። እነዛ እኔን ለሰላምታ ያቀፍክባቸው ምሽቶች ጠረንህ ትዝ ይሉኛል ነገር ግን ደግሞ ይረሱኛል ። እንጃ ባላገኝህ ራሴን እቀበለው ነበር? አላቅም ነገር ግን ፈጣሪ ሊለውጠኝ ፈልጎ በህይወቴ አምጥቶሃል ለዛ ደግሞ ሁልጊዜ ማመስገኛዬ ሆነሃል የህይወቴ አንድ ክፍል ሆነሃል።

አብሬህ መሆን በመፈለግ ወይ በናፍቆትህ ወይ በፍቅርህ አልቃጠልም ምክንያቱም ፍቅር የሚያቃጥል የሚያጠፋ ነገር አይደለም የሚለውጥ እና ውስጥን ሰላም የሚሞላ ኃይል እንጂ። ግን ሁሌ እንደምወድህ ባታነበውም ልነግርህ ፈልጋለው። ከምትወዳት ጋራ የቀና፣ ደስታ ፣ስኬት፣ እና ሰላም ፣ ነፃነት የሰፈነበት ህይወት እመኝልሃለሁ።



# የመሬት መንቀጥቀጥ ያህል:



# ያለይቅርታ ሌላን ማፍቀርን እና መፈቀርን ለተማርኩበት ፍቅር

የኔ ፍቅር

በእጣንና ሰንደል ሽታ የተሞላ እና የተፈጥሮ ብርሀን የሚገባበት ምቹ ክፍል ነው። ግን መልክ አታላይ ነው፤ እዚሁ ክፍል ውስጥ በሳምንት አንዴ የነፍሴን እውነት ለማጋራት እመጣለሁ። ቴራፒስቴ ታጋሽ እና ብዙ ዲግሪዎች ግድግዳዋ ላይ የሰቀለች ተናጋሪ ሴት ናት። የማምነውን እና የምሸሸውን ሁሉ እንድጋፈጥ የሚያስገድዱኝን ጥያቄዎች ትጠይቀኛለች።

ከባድ ስራ ነው። በሀሳብ ደረጃ ሁሌ የማምነው ቴራፒ ጥሩ እና ያለፈ ህይወታችን እንድንረዳ፤ ወደተሻለ ወደፊት እንድንጓዝ፤ ማን እንደሆንን እና እንዴት እዚህ እንደደረስን የምንረዳበት እንደሆነ ነው። ግን ያስፈልገኛል ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ሁሌም የማምነው የተስተካከለ ህይወት ያለኝ፤ የተወሰኑ አነቃቂ መጽሀፎችን ባነብ እና ፖድካስቶች ብሰማ ራሴን ማሻሻል የምችል ሰው እንደሆንኩ ነበር።

ይህ ግን እዚህ ክፍል ያለው ወንበር ላይ እስክቀመጥ ብቻ ነበር። በመጀመሪያ ቀኔ ቴራፒስቴ የሚጠጣ ውሀ አቀብላኝ የማማከር አገልግሎቷን ጀመረች። ምን መጠበቅ እንዳለብኝ አላወኩም። መልካም እና ታጋሽ ሆና ከቴራፒ ምን እንደምፈልግ ጠየቀችኝ። ቴራፒ ምን እንደሆነ ሙሉ ለሙሉ ባልረዳም እውነተኛ ሆኜ መቅረብ እንዳለብኝ ተሰምቶኝ ነበር።

በመጀመሪያ ቀኔ እና ከአገልግሎቱ በፊት በሞላሁት መጠይቅ ላይ በግልጽነት መልሻለሁ። ቴራፒ የእኔ ሀሳብ አልነበረም ግን ለውጥ የሚያመጣ ከሆነ ለመሞከር ዝግጁ እና ጉጉ ነበርኩ።

የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሳምንታት ቀላል እንደሚሆኑ ጠብቄ ነበር፤ ወደዋናው ቦታ ከመድረሳችን በፊት እንደልምምድ ይሆናል ብዬ ነበር። ግን ገና በሶስተኛው ቀን የቴራፒስቷ ጉብዝና ይሁን የእኔ ጎበዝ ታካሚነት ስለራሴ አንድም ሳላስቀር መናገር ጀመርኩ። መናገር እስክጀምር ምን ያህል ነገር ደብቄ እንደኖርኩ አልተገለጸልኝም። አልቅሶ ለማያውቅ ሰው በሚያስደነግጥ ሁኔታ ስቅስቅ ብዬ ማልቀሴን አስታውሳለሁ። ቴራፒስቴ ወፈር ያለ ፎጣ አለበሰችኝ ምናልባትም ህይወት ላይ ተሸክሜ የኖርኳቸውን ትውስታዎች ልታሳስበኝ ይሆናል። የመቅለል ስሜት የሚሰማን ለካ ችግር እንደሌለ በማስመሰል ሳይሆን እንዳለ በማመን ነው።

ያ ቀን የለውጥ ቀን ነበር። በየሳምንቱ እየሄድኩ ችግሮቼን እየቀነስኩ መጣሁ። ቴራፒስቴ እንደተለመደው የቴራፒስት አጠያየቅ በሀሳብ ተውጣ አገጯን እያሸች "ሌላስ የምትነግሪኝ አለ?" አይነት የተለመዱ ጥያቄዎች የምትጠይቀኝ መስሎኝ ነበር። እሷ ግን ካሰብኩት የተለየች ነበረች፤ የራሷን ህይወት እያጋራችኝ ከልምዴ ምን እንደተማርኩ፤ ምን እንዳስታውስ እንዳደረገኝ፤ የት እንደወሰደኝ አይነት ጥያቄዎች ትጠይቀኝ ጀመር።

ሁሉንም ጊዜ መልስ ባይኖረኝም በምክሯ ውስጥ ወደአሳለፍኩት የስሜት ቀውስ እየተጓዝኩ ነበር። ራሴን የሚፈትኑ ጥያቄዎች መጠየቅ ጀመርኩ። ወደእህትና ወንድሞቼ ሄጄ ስላሳለፍነው የልጅነት ጊዜ ጠየኳቸው። ያስቀረሁት ነገር አልነበረም። በቤተሰባችን ፍቅርን ያየነው እንዴት ነው? ወላጆቻችን የገንዘብ ጉዳይ  እንዴት ነበር የሚወጡት? በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው ያደግኩት? የቤተሰባችን ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? ጥሎችን እንዴት ነበር የምንፈታው? የአሁን ማንነቴን እንዴት ያዝኩ?

እድሜ ለቴራፒስቴ እና ጥልቅ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ የሚያስችሉኝን ቃላት መማር ጀመርኩ። የራሴን ዋጋ እንዴት ነው የምለካው; የሚገባኝ እንደሆንኩ እንዲሰማኝ የሚያደርገው ምንድነው; በሰውነቴ የተሸከምኩት ሀፍረት ምንድነው፤ አንዳንድ እውነታዎች ውስጤን ከማናጋታቸው የተነሳ ሆዴን ይገፔ የተቀመጥኩበትን ቀናት አስታውሳለሁ። ተረጋግቼ መመለስ እንድችል ራስን የመግዛት እንቅስቃሴዎችን እያደረግን ሳለቅስ ትዝ ይለኛል። በምችለው ሁሉ ራሴን መረመኩ። እኔን መሆን ምን አይነት ስሜት አለው; የሚገባኝ እና ዋጋ ያለኝ የሆንኩት ለምን እንደሆነ እና ለምን ብዙ ሀፍረት እንደተሸከምኩ ለመረዳት በጣም ከብዶኝ ነበር።


የሚገርመው ሀፍረቴን ባመንኩ ቁጥር በኔ ላይ ያለው ሀይል እየቀነሰ መጣ። ከአመታት በፊት ይህ እንደሚሆን አስጠንቅቀሽኝ ነበር።

በሰው ላይ የምንተራስ እንደሆንኩ እና ለራሴ ዋጋ የምሰጠው ሌሎችን በመርዳት እንደሆነ ተማርኩ። ድርጊቴ ከራስ ወዳድነት የመነጨ አይደለም ብዬ ለማስበው ለእኔ ይህን መቀበል ቀላል አልነበረም። ካለብኝ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ የስሜት መቃወስ የተነሳ ለራሴ ብር ማውጣት የማይገባኝ እንደሆነ እንደሚሰማኝ ተረዳሁ። ጥልን የምሸሽ እና ውስጤ ባይረጋጋም ሰላምን ለመጠበቅ ስልክ ነገሮችን እንደምችል አወኩ። በተወሰነ መልኩ አባቴን እንደምመስል እና የእናቴ ህይወት ከባድ እንዲሆን ያደረጋቸውን ነገሮች እኔም

እንደማደርግም ገባኝ። የስሜት መቃወስ የሚገርም ነገር በዳይም ተበዳይም ያደርጋችኋል። ቴራፒስቴ እንደምትለው በአንድ ጊዜ ሁለት እውነት ሊኖር ይችላል።

የኔ ፍቅር

ቴራፒ በጣም ከባድ ቢሆንም የስሜት መቃወሴን የተጋፈጥኩት ለማሸነፍ ሳይሆን መሸሽ ስላደከመኝ ነው። በተደጋጋሚ ስትነግሪኝ ነበር እኔ ግን ለማዳመጥ ዝግጁ አልነበርኩም። ከባድ ንግግሮችን እንድናደርግ ስትጠይቂኝ ዘግቼሻለሁ። በገንዘብ ማድረግ የምንችላቸው ነገሮችን አላደርግም ብያለሁ። አጋርሽ ሳይሆን ሀላፊነትሽ ሆኜብሻለሁ። በተደጋጋሚ እንዳይሽ እና እንዳዳምጥሽ ጠይቀሽኛል እኔ ግን ላደርግልሽ አልቻልኩም። ቴራፒ ራሴን ዞር ብዬ እንድመለከት እስኪያስገድደኝ ድረስ አልገባኝም ነበር።



አሁን ግን ተረድቼሻለሁ። ታሪክን መቀየር አልችልም- ግን ላንቺ ስል ሳይሆን ባንቺ ምክንያት ተቀይሬ አከብረዋለሁ።

ቴራፒ ያንቺ ሀሳብ ነበር፡ መጀመሪያ ለእኛ ከዛ ደግሞ ለእኔ። የተሻለ እንድሆን ትጠብቂ ነበር። በተሻለ መንገድ አብሬሽ እንድሆን ጠይቀሽኛል። ቴራፒ የጀመርኩት የጥንዶች ቴራፒ ለማድረግ ሀሳብ አምጥተሽ ቴራፒስቷ በመጀመሪያ ከኔ ጋር ብቻ የተወሰነ ጊዜ ማሳለፍ እንደምትፈልግ ስለነገረችን ነበር። የተስማማሁት አንቺን ማጣት በጣም ስላስፈራኝ ነበር። አሁንም ድረስ ቴራፒውን የቀጠልኩት ግን ከረዥም ጊዜ በፊት ያጣሁኋትን እኔን ለመመለስ ነው።

በመጨረሻ ስህተት የሌለበት ሳይሆን ሙሉ ሰው መሆን ራሴን ጨምሮ ሌላን ሰው ለመውደድ እንደሚያስፈልግ ተረድቻለሁ።

አሁንም ብዙ ይቀረኛል። አንዳንዴ ለውጥ በዝምታ ውስጥ ይታያል። ለቅሶን እንደድክመት ሳላይ በማልቀስ፤ ለማስደሰት የምፍጨረጨርላቸውን ሰዎች “እምቢ” በማለት፡ እምቢ በማለት የሚሰማኝን ደስ የማይል ስሜት ከመካድ ይልቅ እንዲሰማኝ ለራሴ በመፍቀድ ውስጥ በዝምታ ለውጤ ይሰማኛል። አንዳንዴ ደግሞ ደምቆ ይታያል። እህትና ወንድሞቼ እናታችንን እንዲንከባከቡ በመንገር፤ መፈጸም ያለባቸውን ክፍያዎች በጊዜ በመክፈል ወይም የረሳሁትን ህልሜን በመኖር ውስጥ አየዋለሁ።

ስለሁሉም ነገር ልክ ነበርሽ። ስለእኛ ብቻ ሳይሆን ስለእኔ። የሚያሳዝነው ይሄን ለመረዳት አንቺን የማጣጥ አፋፍ ላይ መድረስ ማጣት ነበረብኝ። ያገኘሁት ስጦታ ግን አሁን ላይ ምንም ቢፈጠር ራሴን በድጋሚ አላጣም።

ህይወት በየትኛውም ጎዳና ብትወስደን፤ አንድ ነገር ግን አትርሺ። የመሬት መንቀጥቀጥ ያህል ከፍተሽ ያየሽኝ ብቸኛ ሰው ነሽ። ከዛ በኋላ ራሴን መገንባት የኔ ሀላፊነት ነው። ስላየሽኝ አመሰግናለሁ። ራሴን ለመገንባቴ ደግሞ ራሴን አመሰግናለሁ።

“በመጨረሻ ስህተት የሌለበት ሳይሆን
ሙሉ ሰው መሆን ራሴን ጨምሮ ሌላን ሰው
ለመውደድ እንደሚያስፈልግ ተረድቻለሁ።”



# ምስጋና ብርቱ

ለምወዳችሁ ቤተሰቦቼ

አንዳንዴ በምስጋና ተሞልቼ እነቃለሁ። ጉዞዬን ውብ ላደረጉልኝ ሰዎች ሁሉ ከልቤ ማመስገን እንዳለብኝ ይሰማኛል። አክስቴ ለምሳሌ አንዷ ናት። በህይወቴ ውስጥ ሁሌም ብርሀን ሆናኝ አለች። ስለማንነቷ ከነገረችኝ በኋላ የተሰማኝን ግን መግለጽ ያቃተኝን እውነት የምናገርበት በር እንደተከፈተልኝ ያህል ነበር። እውነቷን ስትናገር መስማት ለኔም ሞራል ሰጠኝ፤ ስለራሴ የማውቀውን ግን ቃላት ያጣሁለት እውነቴን እንዴት መናገር እንዳለብኝ ተማርኩ። ከልቤ ማውራት እንድችል እና ራስን ሆኖ መኖር፤ ላመነችበት ነገር ስለመቆም አስተማረችኝ። ጥንካሬዋ ለእኔም ጥንካሬን የሰጠና ህይወቴን የቀየረ ነገር ነው።

ለቤተሰቤ እና ላለሁበት ማህበረሰብ አመስጋኝ ነኝ። ከፍተኛ ብቸኝነት የተሰሙኝ ቀናቶች አሉ ግን በዙሪያዬ የሚደግፉኝ ሰዎች መኖራቸው በጣም ጠቅሞኛል። ራሴን እንድሆን ነጻነት የሚሰጡኝንና የሚያዳምጡኝን የቤተሰቦቼን አባላት እወዳቸዋለሁ። ያለሁበት ማህበረሰብ ውብ ነው፤ እንዳድግ እና ተመሳሳይ ልምድ እና የህይወት ውጣ ውረድን ያሳለፉ ሌሎች ሰዎችን እንዳገኝበት ሆኖኛለሁ።

የጾታ ዝንባሌዬን እንድረዳው ያገዙኝን ጓደኞቼንም ሳላመሰግን ማለፍ አልፈልግም። የስጋ ዘመዶቼን በተለይም አክስቴ ለእኔ ከምንም በላይ ናቸው። ስለማንነት፤ ፍቅር እና ተቀባይነትን ስለማግኘት ብዙ አስተምራኛለች። የምታደርጋቸው ንቅናቄዎች በራሴ ድምጽ እንድተማመን እና ለእውነት እንድቆም ሞራል ሆኖኛል። አብሬያት ጊዜ ማሳለፍ በራሱ አለምን የማይበትን እና እኔም በውስጡ ያለኝ ቦታ የምመለከትበት መንገድ ላይ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ለእኔ ለየት ያለ ብዬ የማስበው ለጥያቄዎቼ መልስ ለማግኘት እና ቤተሰብ ከምላቸው ሰዎች ጋር ደህንነቴ ተጠብቆ መኖር እንድችል ያለኝን ነጻነት ነው።

# ሳደረጉኝ ሁሉ


ፍቅራቸው እና መቀበላቸው ራሴን የማይበትን መንገድ ቀይሯል። ስለብዙ ነገሮች በነጻነት ብናወራም አንዳንዴ በጥያቄዎች እዋጣለሁ። የሁለቱም ጾታ አፍቃሪ በመሆኔ ግራ መጋባት ተሰምቶኝ ያውቃል።  ብዙ ጊዜ በፍቅር ግንኙነት ውስጥ የነበርኩት ከወንዶች ጋር ነው። እናም ራሴን በኩዊር ማህበረሰብ ውስጥ ሳገኘኘው ያስመሰልኩ አይነት ይሰማኛል። ግን ሌሎች ሰዎች ይህ ስሜት ምንም ማለት እንዳልሆነ እና ጾታዊ ዝንባሌዬ የራሴ ምርጫ እንደሆነ ሲነግሩኝ በእጅጉ ቀሎኛል።

በአሁን ሰአት ያለኝ የፍቅር ግንኙነት ከወንድ ጋር በመሆኑ ብዙ ችግር አያጋጥመኝም፤ ብዙዎች የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ መሆኔን ደምድመዋል። ግን ሁሌም ትንሽ ፍርሀት ይሰማኛል። ደህንነቴ አደጋ ውስጥ ወድቆ ስለሚያውቅ መጠንቀቅ እንዳለብኝ ይሰማኛል። የሚቀበሉኝ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ ራሴን በመሆኔ ችግር ውስጥ ልገባ እንደምችልም እረዳለሁ።

ምስጋና በጣም አስፈላጊ ነው። በዚህ ጉዞ ብቻችንን እንዳልሆንን እንዳልረሳ ያደርገኛል። የሚወዱን፤ የሚያስቡልን እና እውነታችንን የሚቀበሉ ሰዎች አሉ። አንዳንዴ በራሳችን አለም እንዋጥና የሚደግፉንን ሳናይ እንቀራለን። ግን ልባችንን ከከፈትን ምን ያህል ሰዎች ሊወዱን እና ከፍ ሊያደርጉን እንደሚፈልጉ ማየት እንችላለን። ይህን ማስታወስ በመቻሌ የእውነት አመስጋኝ ነኝ፤ ፍቅር በዙሪያችንን ስላለ ደስ ይለኛል።

ጊዜ ወስዳችሁ ስላነበባችሁኝ አመሰግናለሁ፤ እናንተም የኔ የምትሉትን ድጋፍ እና ፍቅር እንደምታገኙ ተስፋ አደርጋለሁ፤ መቼም ብቸኛ እንዳልሆናችሁ አስታውሱ። ከፍ ሊያደርጋችሁ በሚፈልግ ድንቅ ቤተሰብ መሀል ናችሁ።

ከፍቅርና ምስጋና ጋር


Betselo
Ohhhh በፀሎት...You're different, to me you're next level of special. Forget about how much I love you because, honestly, I don't even know how to measure it. My betsi, I don't just talk about love. ሳክስ አይደለም, I prove it. I work my butt off literally seven days a week, pulling 98+ hours just so you can feel confident, capable, and comfortable. ከማንም አንሰሽ እንድታይ አልፈልግም . Clothes? Food? Materials ? Happiness? Handled. በጭራሽ እንዳታስቢ You,Your family? Your friends? If they're smiling, I'm winning. I love you so much that I refuse to let your name be in bad stories.
I love you so much that seeing you sad, anxious, or down, makes me stress to find out the reason and need to know why just so i could fix it, because your happiness is my happiness. በፂ when I say I love you...I mean it. I really do. And let's be real nobody, and I mean nobody, loves you like I do. Not even your mama (no offense, mom). I'm your day one, the first person who literally handed over their heart just to see you happy.
So please, I beg you, don't go falling for people who don't love you like I do. Because when you're hurt, I'm hurt and we both know that we don't do well with heartbreak. So, baby girl, listen up, don't keep confusing me following your heart. Just be with me just so we can be at the top of wealth, health, peace...i love you. Deeply, ridiculously, undeniably. And that's that.

በፀሎት ኖርኩኝ
አህ በፀሎት! ልዩ ነሽ! ለእኔ ከምንም በላይ ልዩ ነሽ። ምን ያህል ነው የምወድሽ የሚለውን ባልጀምረው ይሻለኛል ምክንያቱም ቃላት ሊገልጹልኝ አይችሉም። የኔ በጺ ስለፍቅር ማውራት ብቻ ሳይሆን ማሳየት እፈልጋለሁ። በሳምንት 7 ቀን ከ98 ሰአታት በላይ የምሰራው አንቺ በራስሽ እንድትተማመኚ፡ የምትፈልጊውን እንድታደርጊ እና ምቹ ህይወት እንዲኖርሽ ነው። ልብስ፡ ምግብ፡ የሚያስፈልጉሽ እቃዎች፤ ደስታ፤ ሁሉንም ልሰጥሽ ችያለሁ።
አንቺ፤ ቤተሰብሽ፤ ጓደኞችሽ፤ ሁሉም ደስተኛ ናቸው። ታዲያ ይሄ ማሸነፍ አይደለም; በጣም ስለምወድሽ ስምሽ በመጥፎ ታሪክ ውስጥ እንዲነሳ አልፈልግም።
በጣም ስለምወድሽ አዝነሽ፤ ተጨንቀሽ ወይም ደብሮሽ ማየት ምክንያቱን አውቄ እስካስተካክለው ድረስ ሰላም ይነሳኛል።ደስታሽ ደስታዬ ነውና! እወድሻለሁ ስል ከልቤ ነው። እውነት ለመናገር ማንም ሰው እኔ የምወድሽን ያህል ሊወድሽ አይችልም። እናትሽ እንኳን ቢሆኑ (ይቅርታ ማሚ)። የመጀመሪያሽ እና ላንቺ ደስታ ስል ልቤን አሳልፌ የሰጠሁ አፍቃሪሽ ነኝ። እናም እለምንሻለሁ። እንደኔ ሊወዱሽ ለማይችሉ ሰዎች አትውደቂ። ስትጎጂ እጎዳለሁ፤ የልብ ስብራትን ደግሞ እንደማንችለው ታውቂያለሽ። እናም የኔ ውድ ልብሽን እየተከተልሽ ግራ አታጋቢኝ። ከኔ ጋር ሆነሽ የሀብት፤ የጤና እና የሰላም ህይወትን እንኑር።
በብዙ በሚደንቅ እና በማይካድ ፍቅር እወድሻለሁ

**Red**
Hi red tastaweshalesh bechegnenetshen eyasebsh raseshen yetelashebachew gizewoche zare alfewal zare sew nesh zare hiwot aleshe zare leraseshe fker alesh ahun negen begugut yemetetebki lij honeshal tewat kealgash menesaten atferim nege demo kezarewa red yeteshalsh sew tehognalesh yene bale tesfa nurilegne nuroshen edmeshen befker tegbesh antu teblesh belij lij tekebesh erefi

# “ ለራስዎ የፍቅር ደብዳቤ ፃፉ”

**Kidu**
Kiduye ayezosh anchi tenkara nash hulun badel talfiwalsh ☝😍 naw melat erasen

**Gebreala**
አንቺዬ
ስኬት - ማግኘት ብቻ አይደለም።እዉነትን መጋፈጥ ፥ ማጣትንም ማመን ይጨምራል።

ከእለት ትግል የሞኘ ነዉ። ሲሆን - መጨከንም ድል ነዉ። ጨከን በይ😊

**BaKi**

የፍቅርን ሀ ... ሁ ስንጀምር ትዝ ይልሀል? ገና ጨቅላ ህጻናት ፣ ልጆች ነበርን ። ነፍስ ከማወቃችን ስፍስፍ ስልልክ ፣ ስጠነቀቅልክ፣ አይዞህ ከአንተ ጋር ነኝ ስልክ በክፍውም በደጉም አመታትን አልፈን ዛሬም እዚህ አለን ። በደረሰብን ነገር ሁሉ ጥንካሬህን ፣ መልካምነትክን ፣ ለሌሎችም አሳቢ መሆንክን ፣ ባህሪክንና በአጠቃላይ አንተነትህን ወድልሀለሁ ። ሁሌም ያንተው ነኝ:: ዛሬንም በርታልኝ!
አሳቢክና አፍቃሪክ እኔ

**Gloria**

Dear Gloria... You are so beautiful inside and out... I love how you strive to be a better person and how you keep progressing despite all the difficulties and responsibilities life places on your shoulders.. You are strong and smart, and you always find a way to overcome life's obstacles..

I am so proud of the continuous progress you are making in your life..

Keep going, keep fighting... I am certain you will become the woman you've always dreamed of being.

I love you so much...

ግሎሪያ ቪክቶር
ውድ ግሎሪያ .... በጣም ቆንጆ ነሽ ውስጥሽም ውጭሽም ውብ ነው .... የተሻለ ሰው ለመሆን እንዴት እንደምትተጊ እና ህይወት ያሸከመችሽን ችግሮች እና ሀላፊነቶች ለማሸነፍ እና ለማደግ የምታደርጊውን ጥረት አደንቀዋለሁ።

በየጊዜው በምታሳኪያቸው ስኬቶች እኮርራብሻለሁ፡፡
በርቺ፤ መታገልሽን አታቁሚ .... መሆን የምትመኛትን ሴት እንደምትሆኚ እርግጠኛ ነኝ።

በጣም እወድሻለሁ ....